
መለኮታዊ
ኃይል

10 ብር

# መለኮታዊ ኃይል ።

ከተክለ ማርያም ገዛኸኝ

ተ ዘ ጋ ጀ ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም.

በድጋሚ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ታተመ



ደራሲው

# ጸሎት ።

እግዚአብሔር ሆይ ተመስገን ፤ እንደ ቃልህም መሠረት ሕያዋን ስላደረግኸንና ስለምትባርከንም ፤ አሁንም ይህችን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሁሉና ለመላው ኢትዮጵያውያን የመንፈስ ቅዱስ ዝናብህን አፍስስ ። ጸጋህንም አብዛልን ፤ ያለ ነቀፋም መንግሥትህን እንድንጠባበቅ እርዳን ።

በመድኃኒታችን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ፤

አ ሜ ን ።

# መ ቅ ድ ም ።

« መለኮታዊ ኃይል » በሚል ርእስ የጻፍኳት መጽሐፍ ለማንኛውም ክርስቲያን ታላቅ ጥቅምና በረከት እንደምት ሆን በማመን ነው ።

« ከማን ጋር እንደምትሔድ ንገረኝና ማን መሆንህን ልንገርህ » የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር አለ ፤— እንደዚሁም ይህችን መጽሐፍ ለሚያነባትም ሆነ ስትነበብ ለሚያደም ጣት ሁሉ ሁኔታውን ፤ እርምጃውን ፤ ማንነቱን ፤ ገልጻ በፊቱ የምታቀርብ ትንሽ መስተዋት ናት ።

ክርስቲያኖች ያለ ቅድስና መንግሥተ ሰማያትንም ሆነ እግዚአብሔርን ለማየት ስለማይችሉ ፤— በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ቶሎ ሊመጣ ያለውን ክርስቶስን በመምሰል ፤ በቅዱስ ኑሮ ፤ በመጽናት ፤ በእምነት ፤ በፍቅር ፤ በትጋት በአንድነት ፤ነፍሳትን ከሞት ወደ ሕይወት በመመለስ ፤ከአሰ ላፉት ቅዱሳን ጋር ጌታን በአየር ለመቀበል ወደ አየር ለመ ነጠቅ የበቁ ሆነው እንዲጠባበቁ ትረዳቸዋለች በማለት በመ ንፈስ ቅዱስ፤መሪነትና በጾም በጸሎት በመትጋት አዘጋጀኋት።

ስለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ፤ በልሳን ስለመናገርና ጥቅ ሙ ፤ ስለመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሙሉ ፤ ስለ እሥራኤ ልና ጎግ ማጎግ እንዲሁም ስለመጪው ሁኔታቸው ፤ ክርስቶስ ዳግመኛ ይመጣል ስለሚለው ትንቢት እንዲሁም ስለዘመና ችን ሁኔታ ሁሉ ለማወቅ ለምትሹ ሁሉ ይህች ትንሽ መጽ ሐፍ እንደምትረዳችሁ እርግጠኛ ነኝ ።

« መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና ( ወይም በከንቱ ጊዜን ታጠፉላችሁና ) ኤፌ. ፭ ፡ ፲፰ »

## ይህችን መጽሐፍ ፤

ለክርስቶስ ወዳጆች አበረክታለሁ ።

ተክለ ማርያም ገዛኸኝ ።

## አርእስቶች ፤

### ሀ/ ክርስቶስን እንምሰል


፩. ቃል ሥጋ ሆነ ። .. .. .. .. .. ፲፩
፪. የጌቴሴማኒ ልቅሶ ። የጌቴሴማኒ .. .. .. ፲፯
፫. ክርስቶስ በጲላጦስ ፊት ። .. .. .. .. ፳
፬. የኃጢአት ሱስ በክርስቶስ ኃይል ይጠፋል ። .. .. ፳፩
፭. የማይገባህን አትንካ ። .. .. .. .. ፳፯
፮. መዳን በሌላ ስም የለም ። .. .. .. .. ፳፱
፯. እነርሱ አንድ ይሆኑ ዘንድ ። .. .. .. ፴፩
፰. ከተመሠረተው በቀር ሌላ የለም ። .. .. .. ፴፫
፱. ለሚያገለግል ሁሉ የተሰጠ ትእዛዝ ። .. .. .. ፴፬
፲. የእግዚአብሔር መኖሪያዎች ። .. .. .. .. ፴፯
፲፩. አንድነትና ፍቅር ጠፋ ። .. .. .. .. ፴፯


### ለ/ ስጦታህን አትጣል


፩. የአብን የተስፋ ቃል ተቀበል ። .. .. .. .. ፶
፪. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና ጥቅሙ ። .. .. .. ፶፩
፫. ልሳንና ልዩ ዓይነት ልሳን ። .. .. .. .. ፶፯
፬. ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተቀበልናት
ቤተክርስቲያን ምን ዓይነት ነበረች ? .. .. .. ፷፯
፭. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ። .. .. .. .. ፷፯
፮. ጾምና ጸሎት ። .. .. .. .. .. .. ፸፰
፯. ከሥራ የተለየ እምነት ከሥጋ የተለየ ነፍስ ነው ... ፹፫


### ሐ/ ይህን እወቅ አትርሳም ።


፩. ቅዳሚትና እሑድ ። .. .. .. .. .. .. ፹፱

፪. ፍርሃትና ምንጩ .. .. .. .. .. .. .. ፺፩
፫. በረከትህን ቁጠር .. .. .. .. .. .. .. ፺፭
፬. ክርስቶስ በሰማይ ምን እያደረገ ነው ያለው ? ። .. ፺፯
፭. ሰይጣን በእርግጥ እንዳለ እመን ። .. .. .. .. ፻
፮. ፈውስ የልጆች እንጀራ ነው ። .. .. .. .. .. ፻፭
፯. ቃሉን ስበክ በጊዜውም አለ ጊዜውም .. .. .. ፻፱
፰. ክርስቲያኖች ወደ ግብፅ እንመለስ ይላሉ ። .. .. ፻፲፪
፱. ቅድስና .. .. .. .. .. .. .. .. .. ፻፲፯
፲. አሸናፊነት .. .. .. .. .. .. .. .. .. ፻፳፪

መ/ የእግዚአብሔር ቃል ደረጃ በደረጃ ሲፈጸም አስተውል።

፩. እስራኤልና ጠላቶችዋ ። .. .. .. .. .. .. ፻፳፮
፪. ጎግና ማጎግ በእስራኤል ምድር ላይ ። .. .. .. ፻፳፰
፫. ዓለም የሚጠብቃትን ፍርድ ተገንዝባለችን ? ። .. ፻፴፪
፬. ስለዚሁ ዘመን ትንቢቶች ። .. .. .. .. .. ፻፴፬
፭. ከዚህ ቀጥሎ የሚሆን ትንቢት .. .. .. .. ፻፴፮
፮. ኢየሱስ ቶሎ ይመጣል .. .. .. .. .. .. ፻፴፯
፯. መንግሥተ ሰማያት .. .. .. .. .. .. .. ፻፵፪

ሠ/ ከጥፋት ተመለስ ።

፩. ተጠንቀቅ .. .. .. .. .. .. .. .. .. ፻፵፮
፪. ጥያቄና መልስ .. .. .. .. .. .. .. .. ፻፶
፫. ወደ ቃሉ አድምጥ .. .. .. .. .. .. .. ፻፶፬
፬. የሕይወት ታሪኬ ባጭሩ .. .. .. .. .. .. ፻፶፭


# ቃል ሥጋ ሆነ ፤

« የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ፦
ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና ። »
« የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ
የሆነው ክርስቶስ ነው ። » ፩ኛ ቆሮ-፩-፲፰፡፳፬ ።

ጌታ ኢየሱስ ፦እኛን ስለወደደ በአባቱ ዘንድ የነበረውን ክብር ትቶ አንተንም እኔንም ለማዳን ወደምድር መጥቶ ከድንግል ማርያም በበረት ተወለደ ፦ ብርድ አሰቃየው፦ ስለ ሁላችን ይህን ሁሉ ጭንቅ የተቀበለው ፍቅር የሚባል ታላቅ ገመድ ስቦ ስላወረደው ነው ፦

« ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትም ተሞልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጁም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን » ዮሐ. ፩ ፣ ፲፬ ፤

ድንግል ማርያምም «የመውለጃዋ ወራት ደረሰ የበኵር ልጅዋንም ወለደች በመጠቅለያም ጠቀለለችው በግርግም አስተኛችው ፦» « መልአክም ለእረኞች ፦ እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና » አላቸው ሉቃ. ፪ ፣ ፮ ፣ ፯ ፣ ፲ ፤

ክርስቶስ ከሰማይ ከከበረው ቦታ የመጣው አንተን ሊያድን እንደምን የማይመስልህ ይሆን ?

ከሰማይ የወረደው አንተን ወደሰማይ ለመውሰድ ነው ። ከሥጋ የተወለደው አንተን መንፈስ ለማድረግ ነው ። በብርድ

የተጨነቀው የደኸየው አንተን ለማበልጸግ ነው ። የሰው ልጅ የሆነው አንተን የእግዚአብሔር ልጅ ሊያደርግ ነው ። ሰብአዊ ረኃብና ጥማት ያስጨነቀውም አንተን መለኮታዊ ሊያደርግ ነው ። በ፴፫ ዓመት ተኩል ልቅሶውና ስደቱም ፤ አንተን በሰማይ ለዘላለም ሊያስደስት ነው ። የመስቀል ጭንቁ ግርፋቱ፥ ሞቱም ለአንተ ሕይወት ሊሰጥ ነው ። ከመቃብር በመነሣቱም ፤ ያ በስባሽ ሥጋህን ወደማይታይ ሠውሮ ሌላ ክብር የሞላበት የማይሞት ሥጋ መስጠቱ ነው ።

ይህ ነው ለአንተ የመጣ አዳኝ ። የምሥራቹን ተቀበል ፣ ቸል አትበል « ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ ። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ፡— ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ » ሉቃ. ፪ ፥ ፲፫ ፡ ፲፬ ፤

ከእነዚህ የሰማይ ሠራዊቶች ማመስገን የሚገባህ አንተ ነህ ። አንተን የመሰለ ወንበዴና እኔን የመሰለ የኃጢአተኞች ዋና ሊያድን ሲመጣ ፡— ከመጠን ያለፈ ደስታ ሊኖረን ይገባል ።

በምድር ላይ ፴፫ ዓመት ከ፮ ወር ስለኔና ስለአንተ ሲሰቃይ ይህ ነገር ለአንተ ምን ትርጉም አለው ?

## ዮሐንስ ስለክርስቶስ ሲመሰክር ።

ዮሐንስ መጥምቁ በመንፈስ ተመለከተውና በእናቱ ማኅጸን ሳለ እንኳ በደስታ እንደ ዘለለ፡— ከቃሉ ትረዳለህ። ሉቃስ ፩ ፥ ፵፩ ፤

ይህ ዮሐንስ መጥምቁ እንደገና በሥጋዊ ዓይኑ ክርስቶስን አየና ፡— « እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፡— መንፈስ ከሰማይ እንደርግብ ሆኖ ሲወርድ



አየሁ በእርሱ ላይ ኖረ ፤ እኔም አላውቀውም ነበር፡— ዳሩ ግን በውኃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ ፡— መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው ፡— በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ ። እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬአለሁ። » አለ ዮሐንስ ፩ ፥ ፳፱. ፴፪ ፡ ፴፬ ፤

ዮሐንስ የጌታን መንገድ እየጠረገ ሲመጣ አንዳንድ ልበደንዳና ሰዱቃውያን ወደንስሐ ዘወር ሲሉ አየና እናንተ የእፉኝት ልጆች ከሚመጣው ቁጣ ( ከገሃነመ እሳት) እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ ፤ በልባችሁ አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ ፤ አሁንስ ምሳር በዛፎች ሥር ፤ (በኃጥአን ) ተቀምጧል እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ (ሰው) ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል ። ( ማቴ. ፫ ፥ ፯ ፲ ። ዮሐ ፡ ፲፭ ፥ ፩—፯) ብሎ አስጠነቀቃቸው ።

አንተም ምናልባት በዚህ በዮሐንስ ስብከት ውስጥ እንዳለህ ራስህን መርምር ። ሰው ጠማማ ሥራውን እንዲያስወግድ እግዚአብሔር መልእክተኛ ላከልህ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

«እግዚአብሔር አንተንና በዓለም ያሉትን ወደደ፡— በእርሱ ( በክርስቶስ ) የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና ። » ዮሐ ፫ ፥ ፲፮ ፤ የዘላለም ሕይወት እንዳለህ ታውቃለህ ? የመረጥከውን እንድትይዝ ግዜ ተሰጠህ ። ከሞት በኋላ ምርጫ የለም ፣ ዕድል ፋንታህ ዛሬ ብቻ ነው ፤ ንስሐ ግባ ማለት ፡— የኃጢአት ልማድህን ጥለህ ከጌታ ጋር ተጣበቅ ፡— የሚመጣው ቁጣ እንዳይነግሥብህ አምልጥ ። አደጋ በስተኋላህ አታስከትል ። ከጠማማ ልማዶች ተመለስና በሕይወት ኑር ማለት ነው ።

## ሕይወትን ምረጥ ።

«ነገር ግን ታደርገው ዘንድ ቃሉ በአፍህና በልብህ ውስጥ ለአንተ እጅግ ቅርብ ነው ። ተመልከት ፤ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን ፡— ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ ። ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ ፡— ብትታለልም ለሌሎችም አማልክት ብትሰግድ ብታመልካቸውም ፡— ፈጽማችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ » ይላል እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ ። «እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ ። » ዘዳግ. ፴ ፥ ፲፬ . ፲፭ . ፲፯ . ፲፱ ።

ሕይወትን የምትመርጥበት ጊዜ አሁን በዚህች ደቂቃ ነው ፥ ከሁለት ሰከንድ በኋላ የሚሆነውን ነገር አንተ አታውቅም ፡— ጽድቅ ማድረግህ ነው እንጂ ጻድቅ መምሰልህ ለአንተ ጥቅም የለውም ፥ በቅድስና መኖር ነው እንጂ ቅዱስ መምሰል ለአንተ ረብ የለውም ፥ ማመንህን በመንፈስ ማረጋገጥ ነው እንጂ በከንፈር ማመንህ ዋጋ አያስጥህም ፡— ሮሜ ፰፡፲፯ ፤

«እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ ፤ መልካም ታደርጋለህ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል ያዕ- ፪ ፡ ፲፱ እምነትህ በመልካምና ቅድስና በተሞላበት መብራት ካላንጸባረቀ በተራራ እንዳለች ከተማ ጎልቶ ለክርስቶስ ካልታየ ዋጋ የለውም ። እኛ ጥለነው እንደምንሄድ ቆሻሻ ነገር ነው ። እንዲህ ያለ የመምሰል ጽድቅ ሁሉ ለእግዚአብሔር ስለሚገማው ሽታውም እጅግ አስቀያሚ ስለሆነ ከዲያብሎስ እምነት ጋር ወደ ገሃነም ይጥለዋል ።

አንዳንድ ሰዎች የክርስቶስን በምድር ላይ መዋረድ መሰደድ ፡— መገረፍ ፡— መስቀልን መሸከም ስለግል ደኅንነታ



ቸው ሲል በመስቀል መቸንከሩን ፍጹም አልተቀበሉትም ዘንግተውታል ።

እንዲህ ያሉ ሰዎች በሞቱ ቤተ ክርስቲያንም ይገኛሉ ። ክርስትያን ነን ይላሉ ፤ ዳግም ግን አልተወለዱም ሃይማኖት ያላቸው ይመስላሉ ፡— አንዲት ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ አያምኑም ። ከዓለም ተለይተናል ይላሉ ዓለም የሚያደርገውን ግን ያደርጋሉ ። እሑድ ጥዋት በዘልማድ ቤተ ክርስቲያን ይገኛሉ ። ከግንቡ የተሻለ ጽድቅ የላቸውም ጽድቃቸው ዡነኔ ሆነባቸው ። ንስሐ ገብተው እንዳይመለሱም ኃጢአትና የኃጢአት ፍቅር ዓይኖቻቸውን አሳወረባቸው ወደማይፈልጉትም በየደቂቃው እያቅበዘበዘ ወሰዳቸው የኃጢአት ብዛትም ሰላም ነሣቸው አስጨነቃቸውም ።

ክርስቶስ ለእንደዚህ ያሉ ሰዎች መምጣቱን አልተገነዘቡም ማለት ነው ? አስተማሪ አጥተው ይሆን ? በእርግጥ አስተማሪ ያጡ ይመስላል ። በሌላ በኩልም ደግሞ አስተማሪ ያጡ አይመስሉም ።

«እውነት እላችኋለሁ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው ። » ማቴ. ፲፰ ፥ ፫. ፬ ።

አንተም ሌላው ኒቆዲሞስ ሳትሆን አትቀርምና ጌታ መምለስ እንዳለብህ ያስጠነቅቅሃል ። ሰው ካለበት ትውልድ ወደ አዲስ ትውልድ ካልተሻገረ በቀር በሰማይ ቦታ የለውም። ከአሁን ቦታህ ፡— ከምትጓዝበት የጥፋት መንገድ ካልተመለስክና የመንግሥተ ሰማያትን መንገድ ካልያዝክ በክርስቶስ መንግሥት ክፍል የለህም ።

ክርስቶስ ፡ —«ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ። ከሥጋ የተ

ወለደ ሥጋ ነው ፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው ። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ ይልሃል ። ዮሐ ፫ ፣ ፭—፯ ከአዳማዊ ሕይወት ወደ ክርስቶሳዊ ሕይወት ከአዳም ደም ወደ ክርስቶስ ደም መሻገር ይሻልሃል ። ፩ ቆሮ ፲፭ ፣ ፵፯-፵፱ ።

« ክርስቶስ ከሰማይ የወረደው በራሱ ፈቃድ አይደለም እግዚአብሔር ልኮታል እንጂ ፤ እግዚአብሔርም ፡—ልጁ በብዙ ወንድሞች ( በእንተም ) መካከል በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና » ሮሜ ፰ ፣ ፳፱ ፤

ስለዚህ እንደገና ሳትወለድ ክርስቲያን ነኝ እያልክ የቤተ ክርስቲያንን ወንበር ብታሞቅ እንዲሁም የመዝሙር መጽሐፍት ብታስረጅ፡— አንተንም አይተው የሚደናቀፉ ሰዎች ብታበዛ -በአንተ ዓለማዊነት ብዙ ቢሰናከሉ ፤ ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ ተሸክመህ ወደ ባሕር ወደ ነበርክበት ጥፋት ብትገባ ይሻላል ። ክርስቶስን እንደገና ማሰቃየትህ ነው ። ትስቅለውማለህ ።

ተመለስ ልብህ በያዘው ቆሻሻ ነገር አይኩራ « ነገር ግን ጸጋን አብልጦ ይሰጣል ፡—ስለዚህ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሑታን ግን ጸጋውን ይሰጣል ይላል እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል ። ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደእናንተም ይቀርባል ። እናንተ ኃጢአኞች እጆቻችሁን አንጹ ፤ ሁለት አሳብ ያላችሁ እናንተ ልባችሁን አጥሩ ተጨነቁና እዘኑ አልቅሱም ። ሳቃችሁ ወደ ኃዘን ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ ። በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል» ይላልና ። ያዕ. ፬ ፣ ፮-፲ ፤



## የጌቴሴማኒ ልቅሶ ።

የጌቴሰማኒን ልቅሶ አስበው ። የደም ወዙንም አትርሳ «ተንበርክኮም ፡—አባት ሆይ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር ፤ ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታው መልአክ ታየው በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር ። ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ ። » ሉቃ .፳፪፡ ፵፪—፵፬ ፤

የአንተንና የኔን ኃጢአት ተሸክሞ ሲጣጣር ተመልከተው፡፡የኔንና ያንተን ኃጢአት ሊያስተሠርይ የሚችል ሌላ ኃይል አልተገኘም ሙሉ ሌሊት ተንበርክኮ ሲያለቅስ አይተህ ካልተመለስክ በምን መሣሪያ ልትመለስ ትችላለህ ? ስለአንተ ኃጢአት ሲጮህ ሲያለቅስ ሲጣጣር « ሸክሙ ከበደኝ ከእኔ ውሰድ » እያለ ወደአባቱ ሲጣራ እየሰማህ ካልተመለስክ የትኛው ሰባኪ እንዲመልስህ ትጠብቃለህ ?

እነሆ የመዳንህ ፣ የመመለስህ ፣ የእንደገና ተወልደህ ሰማያዊ ውልድነት ማግኘትህ ቀንና ደቂቃ አሁን ነው ። ፪ኛ ቆሮ.፮ ፣ ፪ ። ነገ የአንተ አይደለችም እኛ የትናትና ብቻ ነን ። ከደቂቃ በኋላ ስለሚሆን ነገር ፈጽሞ አታውቅም ስለዚህ ራስህን አድን ከሚመጣው ቁጣ ዳን ።

### በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ ።

አንዳንድ ይሁዳዎች በቤተ ክርስቲያኖች አሉ ።

ይሁዳ ጌታችንን ለ፴ ብር የሸጠው ሌባ ስለነበረ ነው ። «ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለነበረ ነው ። » ዮሐ.፲፪፡፮ ፣ አንተስ ይሁዳን ትመስላለህን ? የክርስቶስን ገን

ዘብ ትሰርቃለህን ? ራስህ የክርስቶስ እንደሆንክ ዘንግተኸዋ
ልን ! የራስህ እንደሆንክ ቈጥረህ በሥጋህ ላይ አመፅ ታደር
ጋለህን ? የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ትንቃለህን ? ቸልተኞችን
ቸልተኛነት ይገድላቸዋል ተብሏል ።

« ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእና
ንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታ
ውቁምን ? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም
ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ ። » ፩ኛ ቆሮ፮፣ ፲፱-፳፣
አንተም በተገዛው ሥጋህ ላይ ሥልጣን የለህም ።

«ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና
እነዚህ እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ ስለዚህ በሥጋችሁ የም
ትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም » ይላል ገላ፣ ፭ ፣ ፲፯ ፤

ይሁዳ በሥጋው የተሰማውን አደረገ ፤ ሞተም ። አንተም
በሥጋ የተሰማህን ያህል ብታደርግ በክርስቶስ ደም የተገዛ
ውን ሥጋ ስለምታጠፋ ወዮልህ ። ሁለተኛ የክርስቶስን ሥጋ
በጦር መውጋትህ ነው ። አንዳንዶች ትዕቢተኞችና እንቢተ
ኞች ክርስቲያን ነን እያሉ በሥጋቸው አመፅ ያደርጋሉ ። የጸ
ጉራቸውን ብጣሽ መልሰው ለመትከል የማይችሉ ፤ ሳንባን የመ
ሰለ ታላቅ የአካላችን መንቀሳቀሻ በትንባሆና በሲጃራ እቃ
ጥለው ወንፊት እስኪመስል በሲጋራ መርፌ ቀዳዳዎች ይፈ
ጥሩበታል አንጀቶቻቸውንም በመጠጥ ቢላዋ ይልጣሉ ፡—
በራሳቸው ጥፋት የክርስቶስን ንብረት ይሰርቃሉ ፡— እንደ
ይሁዳ ሌቦች ነፍሰ ገዳዮች እያሉ ጥፋት የሌላቸው ንጹሐን
መስለው በቤተ ክርስቲያን ይቀመጣሉ ። መንፈሳዊ ስብሰባ
ዎች ይመራሉ ፡— ይዘምራሉ ክርስቶስን ያስድባሉ ወንጌል
ንም ያረክሳሉ ። ያልጸኑትንም ያሰናክላሉ ፤ ነፍሳትን ለማጥ
ፋት ሰይጣን የቀጠራቸው ናቸው ።



እንደነዚህ ሰዎች ነኝ የምትል ከሆነ ተመለስ አለበለ
ዚያ በአንተ ምክንያት በእምነት ሕፃናት የሆኑት ከሚጠፉ
ትልቅ ወፍጮ ተሸክመህ ወደ ነበርክበት ጥልቅ ባሕር መግ
ባት ይሻልሃል ። ተው ፤ ብዙዎች ባንተ ጠፍተዋል ፤ ስለዚህ
ይብቃህ በቤተ ክርስቲያን ፊት ቆመህ ተናዘዝና ይቅርታን
ተቀብለህ ተመለስ ፤ ራስን እንደ ሕፃን ማዋረድና መመ
ለስ ማለት እንዲህ ነውና ። በተሰበረ ልብ መመለስህ በኑዛዜ
ስትመለስ ብናይ ነው ። ክርስቲያን መሆናቸውን በፍሬአቸው
ይታወቃሉና ፍሬህን አሳይ ፤ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፯
ያለች ኃጢአተኛ የነበረች ሴትዮን ተመልከት ፤ በልቅሶ በመ
ረረ የመመለስ ኃዘን ስለተመለሰች ብዙ ኃጢአትዋን ወዲያ
ውኑ አስተሰረየላት በሰላምም ሞልቶ ሸኛት ፤ ለአንተም እን
ዲሁ እንዲያደርግልህ «ዛሬ ና » እያለ ይለምንሃል ፤ ተመለ
ስና በሕይወት ኑር ።

ክርስቶስም፡— እኔን ፈልጉ በሕይወትም ትኖራላችሁ በሕ
ይወት ትኖሩ ዘንድ መልካሙን እንጂ ክፉን አትፈልጉ ይላል
አሞጽ ፭፣ ፬፡፲፬ ፤ አንተም ሕይወት እንድታገኝ ክርስቶስ ስለአንተ
በመስቀል ሞተ ። የሞት ተቃራኒ ሕይወት ነው ። ስለዜህ
አንተ ከሞትክ በአንተ ሕይወት ስለማይገኝ ተመሳሳይ የዘለ
ዓለም ሞት ብቻ ትወርሳለህ በጌታ ሞት አምነህ ካለብህ
ደዌ ለመዳን በደሙ ብትታጠብ ግን አሁን ትነፃለህ ።

የዓለም ሳሙናና እም በሙሉ ቢሰበሰብ በውቅያኖስ ያሉ
ውኃዎችም በቧምቧዎች በላይህ እያፈሰስን በቡሩሽ ዕድሜህን
ልክ ብናጥብህ መጥፎ ተግባርህ ከፉ ልማዶችም ሆኑ ኃጢ
አትህ ሊታጠብ አይችልም ። ማንኛውም የዓለም ዶክተር
ሊመረምረው የማይችል የኃጢአት መከማቻ ልብህን ሊፈውስ
የሚችል ኢየሱስ ብቻ ነው ። ስለዚህ በፍጹም ሱባኤ ወደ
ክርስቶስ ተመለስና በሕይወትህ ሁሉ ተገዛለት ።

## ክርስቶስ በጲላጦስ ፊት ፤

### ለፍርድ ከቀረበ በኋላ ሲጨክኑበት ።

ስለ አንተ ኃጢአት ሲል ክርስቶስ በፍርድ ወንበር ቀረበ። ይኸውም አንተ እንዳትፈረድ ነው ፤ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አል ላከውምና ። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም ፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈ ርዶበታል ። » ዮሐ፤ ፫ ፤ ፲፯.፲ ፰ ፤

የሚያምን ለፍርድ በሰማይ አይቀርብም አንዴ ክርስቶስ ተፈርዶለታል ። (ጲላጦስ ፈራጅ ክርስቶስ ተፈራጅ) ሰው ከሳሽ እግዚአብሔር ተከሳሽ ፡— (በርባን) ሲመሰክርለት ክርስቶስ ሲመሰክርበት የዋለው አንተን ነፃ ለማድረግ ነው ። እወቅ — ተቀበለው ፡—እመንበት ፡— አምልከውም ። በሰማይ ታገኘዋለህ ።

ክርስቶስ ጀርባውን ለገራፊዎች ፡— ጉንጩንም ለጠጉር ነጪዎች ሰጠ ። በፊቱም ተተፋበት ። ኢሳ.፶ ፤ ፮ ። እነርሱም ሞት ይገባዋል ብለው ጮሁ በዚያን ጊዜ በፊቱ ተፉበት ጐሰ ሙትም ሌሎችም በጥፊ መትተው ትንቢት ተናገር በጥፊ የመታህ ማነው እያሉ ቀለዱበት ። ማቴ.፳፮ ፤ ፷፮-፷፰ ፤ በዚህ ሁሉ ግርፋትህን ተቀበለልህ የዘላለም ውርደትህንም ተሸከ መልህ አንተ ለዚህ ምን ትላለህ ? ምን ስሜት አለህ ? ስለ ተቀበለው ፍርድ አስብ ።

ወዳጄ ክርስቲያን ነኝ ባይ ሆይ እይ ወደቆሰለው እጁ እግሩ፡ጐድኑ ፤ ራሱም ስለአንተ እንዲህ ተጨንቆ አንተን ለማዳን እንዲህ ተጐሳቁሎ አንተ ግን እስከ አሁን ኃጢአት ትበላለህ ፡— እንደ ብዛታቸው መጠን ኃጢአት ሠሩብኝ ።



እኔም ክብራቸውን ወደነውር እለውጣለሁ ። የሕዝቡም ኃጢአት መብል ሆኖላቸዋል ልባቸውንም ወደበደላቸው አድርገ ዋል እንደሕዝቡም እንዲሁ ካህኑ ይሆናል፤ በመንገዳቸውም እበ ቀላቸዋለሁ ሥራቸውንም እመልስባቸዋለሁ እግዚአብሔርንም መጠበቅ ትተዋልና ሲበሉ አይጠግቡም ሲያመነዝሩም አይ በዙም ይላል ። ሆሴዕ ፬ ፤ ፯-፲ ።

ከምታደርገው ግፍ ካለህበት ብድግ ብለህ በቅጽበት ተና ዘዝና ተመለስ ፤ ሞትን አትምረጥ ። ሕይወትን ብቻ ምረጥ የያዝከው በጣትህ ላይ ያለውን እርኩስ የሕይወትህን ጠንቅ ጣለው ጌታ ይጠራሃልና ቶሎ ብለህ ተመለስ እንደ ይሁዳ አስ ቆሮቱ የብር ወዳጅ አትሁን ፤ ብር ብር ብለህ አትጥፋ ገን ዘብ የኃጢአት ሁሉ ሥር ነውና በገንዘብ ገመድ ታስረህ አት ጥፋ ተመለስ ። ክርስቶስ ይጠራሃልና ።

## የኃጢአት ሱስ በክርስቶስ ኃይል ይጠፋል

አንተን ደግሞ ሌላ አመል አስሮታል እያሉ ያወሩብሃል እውነት ይሁን ውሸት አንተና ክርስቶስ ብቻ ታውቃላችሁ። ይኸም ሆኖ አዘውትሮ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል በመዝሙር በስብከት በምጽዋት ሰብሳቢነት በአሥራት መክፈል በኩራ ትን በማውጣት ቤተክርስቲያንን በሐሳብ መርዳት እንደዚህና እንደዚህ በመሳሰሉ ጠቃሚ ነገሮች ተሳታፊ ነው ይሉሃል ፤ እውነት ነው ውሸት ! ።

ወዳጄ ሆይ ፤ እንደነዚህ ያሉ ነገሮች በማድረግ ከሚመ ጣው ቁጣ ለማምለጥ አትችልም ። ፍጹም አትችልም ይል ቅስ የክርስቶስን ምክር ብትሰማ የተሻለ ነው ።

ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር ማለት ከመንፈስ ከላይ ካልተወለደ በቀር የሰማይ ቤት ሊወርስ አይችልም እያለ ዴጋግሞ ያስጠነቅቅሃል ዮሐ.፫ ፣ ፫-፭ ፤ ዳግሞ መወለድህን ማረጋገጥ አለብህ። ባለህበት ቆም በልና ስለ ሕይወትህ አስብ ።

ዳግም መወለድ ማለት ምን እንደሆነ ከ፪ኛ ቆሮ ፭ ፣ ፲፯-፲፰ ተመልከት፡- ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ። አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል ። ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ከአስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው ይላል።

አሁን ስለ እንደገና መወለድ ሳይገባህ አይቀርም ይመስለኛል እንደገና መወለድ ከነበረህ አሮጌ አዳም ወደ ሰማያዊ ትውልድ ስትለወጥ ነው ። ይህ ለውጥ የሰው ኃይል የማያደርገው ነው ። በመንፈስ ቅዱስ በጌታችን በኢየሱስ በሆነ ለውጥ ነው እንጂ የሚከተለውን ቃል አስተውለው ።

« አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል እርሱ ሰላማችን ነውና ፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ያስታርቅ ዘንድ ነው ።

በእርሱ ሥራ ሁላችን (ያመነው) በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና እንግዲያውስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና ( ያገራቸው ልጆች ) የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም ይላል » ። ኤፌ. ፪ ፣ ፲፫ - ፲፱ ፤



ስለዚህ ምክንያት ዛሬ መለወጥ ትችላለህ ባለህበት ቦታ ከታቻለህ በጉልበትህ ተንበርክከህ ከልብህ ወደ ክርስቶስ አልቅስ በዚህ ቅጽበት ከሚያስቸግርህ የሥጋ ኃይል ሊያላቅቅህ ፈጽሞ ይችላል ፤ ለጌታ የሚሳነው የለምና በመንፈሱ ሞልቶ አዲስ ሕይወት ይሰጥሃል ። ሊለውጥህ የሚችል የእግዚአብሔር ሥራ ነው እንጂ የአንተ ተግባርና ኃይል አይደለም ። ዳግመኛ ካልተወለድህ ካለብህ የሞራል ጉድለት ልትፈወስ አትችልም ። በቤተክርስቲያን በመዘመርህ በመገኘትህ ወይም ለቤተ ክርስቲያን መልካም በረከቶች በመስጠትህ እንድትድንና ከሚመጣውም የኃጥአን ቦታ ሊለይህ አይችልም ። በምታደርገው ሥራ ብቻ ለጽድቅና ለቅድስና ለመንግሥተ ሰማያት ተስፋ ማድረግ ዕውር ያለመሪ በገደል አፋፍ እንደሚንሸራሸር ነው ኤፌ ፪ ፣ ፰-፲ ፤

እስቲ ወደመስቀሉ ተመልከት ፡— ጉድለትህ እዚያ ተሰቅሎአል ። ጌታን መስቀልን አሸክመው ወደጎልጎታ ሲወስዱት ተመልከት ሕዝቡም ሁሉ ደሙ በእኛና በልጆቻችን ይሁን ስቀለው ! ስቀለው ! እያሉ ሲጮሁ አስተውል ። አንተስ ከእነርሱ የምትሻልበት በምንድርነው ? በኃጢአት ያሉም ሰዎች ሁሉ አንተም አብራችሁ ሰቃዮቹ መሆናችሁን መገንዘብ አለብህ ። በኃጢአትህ ተጸጽተህ መመለስ ግድ አለብህ ።

ስለአንተ «ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት ፣ ከእሾህም አክሊል ጉንጉነው በራሱ ላይ በቀኝ እጁም መቃ አኖሩ » ይህ የሆነው ለአንተ የሕይወትና የሰላም ዘውድ የጽድቅንም ብትር ለማጐናጸፍ ነው ። «ዘበቱበት ተፉበትም መቃውንም ይዘው ራሱን መቱት ቀዩን ልብስም ገፈፉት ሊሰቅሉትም ወሰዱት » ይላል ማቴ. ፳፯ ፣ ፳፰-፴፩ ፤

ከዚህ የባሰ ውርደት በአይሁድ ጊዜ አልነበረምና እስኪበቃቸው ድረስ የሕይወትን ጌታ አሰቃዩት በዚህም ቅር

ሳይለው በእርሱ የሚያምኑትን ሊቀበሉት ላለው ክብር ለማ ስገኘት የመስቀልን ጽዋ ጠጣው ፤ ጨለጠውም ፤ ሞተ ፤ አንተንና እኔንም ሕያዋን ሊያደርግ ከሐፍረትም ሊያድን ነው ።

ስለ አስጨናቂዎቹ ሕይወት በዚያች በዓርብ ዕለት ፡— እንደተጨነቀ ተመልከት ፤ ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ ።

ፀሐይም አምላክዋን እንደምታውቅ መሰከረች የሁሉ ጌታ ለመስቀል ሞት እንደጨከነበት አውቆ ክርስቶስ በፍጹም ሥጋነቱ «አምላኬ አምላኬ ለምን ተለየኸኝ» አለ እኛን ለማስ ታረቅ ፈጽሞ ለመስቀል ስቃይ ተለይቶት ነበርና ፡— በዚህ ስቃይ ነው ያንተን የኃጢአት ሱስ ሊያጠፋልህና ከረከሱ ሥራ ዎችህም ሊለውጥህ የሚችለው ። ቅረበው ይቀርብሃልና ።

የቤተ መቅደስ መጋረጃ የሰማይን ቅድስተ ቅዱሳን መው ረሳችንን ለመግለጽና በኃጢአት ምክንያት የነበረውን ልዩነት እንደተደመሰሰ ለማስገንዘብ ማንም ሳይቀደው ከላይ እስከታች ከሁለት ተተረተረ ። በደልህም ሁሉ አብሮ ተደመሰሰልህ። እሰይ በል እንደተደመሰሰልህም እመን ። በደስታም አመስግን ።

ምድር ተናወጠች ፤ ፈጣሪዋን ታምናለችና አለቶች ተሰ ነጠቁ ፤ መቃብሮችም ተከፈቱ የሲኦል አሸናፊ የሞት ድል አድራጊ እንደመጣባቸው ተገንዝበዋልና ። ተኝተው ከነበሩብ ትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ ከትንሣኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ ኢየሱስ ትንሣኤና ሕይወት እንደሆነ ተሰብኮላቸው ነበረና ።

« የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ፡— ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና » ፩ኛ ቆሮ. ፩ ፥ ፲፰ ፤



« በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽ ፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ» ገላ. ፫ ፥ ፲፫—፲፬ ፤

አንተ ራስህ በርባን ነበርክ ግን ክርስቶስ አንተን ከመ ስቀል አስጥሎ በመስቀል ተኮነነልህ በሰው ተረገመ ኮነኑ ትም ።

« ክፉ ከሆነው ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አም ላካችንና እንደአባታችን ፈቃድ ስለኃጢአታችን ራሱን ሰጠ ። ለአብ ከዘላለም እስከዘላለም ክብር ይሁን ። አሜን ።» ገላ. ፩ ፥ ፬—፭ ፤

ሁለት አጥፊዎች በጥፋታቸው ተሰቅለው የሚቀልዱትን ተመልከት ፤ በመሃከል የተሰቀለው ግን ስለበርባን ብሎ ነው ይኸውም አንተና እኔ ነበርን ልንሰቀልበት የሚገባን ።

ክርስቶስ በእኔና በአንተ ፋንታ ሲሰቀል ከእርሱ ጋር ለተሰቀሉትም ተሰቅሎ ነበር ። ሁለቱም ስለ ክርስቶስ ያውቁ ነበር ግን ከሁለቱ አንዱ ስለሚመጣው ስለከፋው የፍርድ ወንበርና የገሃነም ቃጠሎ አሰበ ወደጌታም ዘወር አለና እን ዲህ አለ ፡—

ጓዴ ሽፍታ ሆይ ፡— «አንተ እንደዚህ ባለፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን ? ስለ አደረግነውም የሚ ገባንን እንቀበላለንና በእኛ እውነተኛ ፍርድ ነው ፤ ይህ (ክር ስቶስ) ግን ምንም ክፉት አላደረገም ብሎ ገሠጸው ። ኢየሱ ስንም ፡— ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው ። ኢየሱስም «እውነት እልሃለሁ ፡— ዛሬ ከእኔ ጋር በገ ነት ትሆናለህ አለው » ሉቃ. ፳፫ ፥ ፴፱—፵፫ ፤

ሌላው ሽፍታ ወይም ነፍሰ ገዳይ ግን « አንተስ ክር
ቶስ አይደለህምን ? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው ።
ሉቃ . ፳፫ ፣ ፴፱ ፤
አንተም በተግባርህ በማስመሰልህ ለሌሎችም . እንቅፋት
በመሆን የክርስቶስ ገንዘብ ነፍሳት በማጥፋት ለክርስቶስ እሠ
ራለሁ በማለት በማታለል ጻድቅ ሳትሆን የጻድቃን መሳዮች
ልብስ በመልበስ ወይም በጻድቃን ሥፍራ በመገኘት ክርስቶ
ስን ትሰድብና ታሰድብ ይሆናል ። በፍርድ ውስጥ በሚያሰቃይ
ፍርድ ውስጥ ሳለህ በነፍስህ ትቀልዳለህን ? አትመለስምን ?
ራስህን አዋርድ ጌታም ከፍ ያደርግሃል ። እንዲህ ከሆንክ በጥ
ፋት አለህና ዛሬ ሁሉን ጥለህ የሥጋ ክብርን ጥለህ ነፍስህን
ብታድን ይሻልሃል ሰላም ከሌላቸው ጋር አትተባበር ።

በክርስቶስ ፊት ስትቀርብ ጻድቅና ቅዱስ መስለህ በመ
ታየትህ ልትድን ትችላለህ ብሎ አይፈርድልህም ፤ እንኳን አንተ
አንድ አጋንንት አውጥተህ የማታውቅ ዘመናቸው ሙሉ በክ
ርስቶስ ስም በማመን በተሰጣቸው የአጋንንት ማስወጣት ሥል
ጣን ሲያስወጡ የነበሩ አገልጋዮች እንኳ ሳይገነዘቡት ባደ
ረጉት አመፅ ሲባረሩ ተመልከት ።

«በሰማያት ያለው«የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ» ጌታ
ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደ
ለም ። በዚያ ቀን ብዙዎች ፡— ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ
ትንቢት አልተናገርንምን ? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን ?
በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንም ? ይሉኛል የዚያን ጊዜ
ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመ
ሰክርባቸዋለሁ » ይላል ክርስቶስ ራሱ ። ማቴ. ፯ ፣ ፳፩—፳፫ ፤

ከሚያምኑት በቀር በስሙ ተአምራት ለማድረግ ትንቢት
ለመናገር አጋንንትን ማስወጣት የሚችሉ የሉም ማር. ፲፮ ፣ ፲፯
ከየትኛው ክፍል ነህ ? በክርስቶስ ትቀልዳለህን ? ስለዚህ ማቴ
ዎስ ፯ ፣ ፳፩—፳፫ ፤ የሚያስጠነቅቀው እኔንና አንተን ነው ።



አስተውል እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይጥላቸዋል በመም
ሰል ብቻ የክርስቶስ የሆኑትም በሰማይ ቦታ የላቸውም ። አን
ተም ልታደርገው የሚገባህ ዕለት ዕለት በሚያጠራ ሳሙና
ከእድፍህ መንፃት ነው ፡— ኃጢአትን ሊያነፃ የሚችለው
ሳሙና ደግሞ የክርስቶስ ደም ብቻ ነው ። ምሕረት እንደጠየ
ቀውና እንዳገኘው ሽፍታ እንጂ እንደ ቀልደኛው ነፍሰ ገዳይ
ራስህን አትበቀል ።

## የማይገባህን አትንካ

ነገር ግን አስተውል ይህ ሳሙና በእጅህ ያለውን ግማት
እንደሚያስወግድ ከመገንዘብህ በፊት ሳሙናውን ወስደህ ብት
ጠቀምበት በዕዳ ላይ ዕዳ መጨመርህን እወቅ ፡— ወደሚከተለው
ጥቅስ ተመልከት ፡—

« ይህንን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠ
ጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና
ስለዚህ ሳይገባው ፤ ( እንዘ ኢይደልዎ ) ይህን እንጀራ
የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ
አለበት ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ
ከጽዋውም ይጠጣ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ
ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና ። (ሳይገባቸው
የበሉና የጠጡ ) ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ
ብዙዎች አሉ አያሌዎችም ( ሞቷል ) አንቀላፍተዋል ። ራሳ
ችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር ። » ይላል ።
፩ኛ ቆሮ. ፲፩ ፣ ፳፮—፴፩ ፤ ቅዱሱን ስጦታ ከኃጢአታችን ጋር
ሳለን እንንካው ።

ወዳጄ ፡— የክርስቶስ አባል ሳትሆን የቤተ ክርስቲያን
አባል በመሆን የክርስቶስን አካል ወይም ሥጋ ለመውሰድና ክ
ስቶስን መምሰል በደሙም አንድ መሆን አትችልም። ሃይማኖትን
መቀበልና ክርስቶስን መቀበል አንድ አይደለም በዚህ ተጠንቀቅ።

በቀራንዮ ቦታ በመስቀል ተሰቅሎ ሳለ የተናገረው ቃል ትገዝ ይበልህ ።

« አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ » ካለ በኋላ አንተንና እኔንም ለማዳን እጅግ በመጠማቱ « በዚያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበርና ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ ተፈጸመ አለ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ ፤» ዮሐ. ፲፱ ፡ ፳፰—፴ ፤

ይህን አዳኝ ትመለከተዋለህን ? የተጠማው ውኃ ሳይሆን የአንተን ነፍስ ነበር በፍቅሩና በምሕረቱም ብዛት ከሥጋቸው ያለውን ደዌ እያስወገደ በልባቸው ያለውን ደዌ ወደሚያስወግድበት ወደ ፍጹም ዓላማ ወደመስቀል የአንተን መርገም ለመሻር ( ለመፈጸም ) ወጣ በዚያም የአንተን ጥማት አረካ አጠገብህ የማይጠፋ ምንጭ ከፈተልህ ይህንን የሕይወት ምንጭ ሲከፍትልህ «ተጠማሁ» አለ በልብህ የነበረውን መራራ ኃጢአትህን ጠጣው ፤ የአንተንና የእኔን ኃጢአት ገነደሰው ።

መድኃኒትህ ስለአንተ ሞተ ፣ አንተን ለማርካት ተጠማሁ እያለ በታላቅ ጭንቅና ጩኸት ነፍሱን ለአንተ ሰጠ ፣ ይህን ያህል ታላቅ ስጦታ ሳትገነዘብ የክርስቶስን ሥጋና ደም ብትወስድ የክርስቶስን ሥጋና ደም ከፍየል ሥጋና ደም ስላልለየኸው አስቀድሞ የሥጋ ደዌና ሞት ሁለተኛ ደግሞ የዘላለም ሞት ዕዳ አለብህ ፤ ራስህን መርምር ራስህን ብትመራመርና ከማን ጋር እንደምትተባበር ከተገነዘብክ ግን ፡— ከፍርድ ነፃ ትሆናለህ ። አስተውል ፡— የአንተ ሥጋ ነበር ከክርስቶስ ጋር በመስቀል የተሰቀለው የአንተ ሥጋ ነበር በመስቀል የሞተው ስለዚህ ነው ጳውሎስ « መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል ። እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደሞታችሁ ግን



በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ » (ሮሜ ፮ ፡ ፲—፲፩) የሚልህ ።

የአንተ ሥጋ በመስቀል ከሞተ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ተሠውሯል ለኃጢአት እንግዲህ ሕይወት የለህም የተጣለውን የአዳምን ሥጋ ደግመህ ለማምጣት ወደተፋኸው አትመለስ ። በእርግጥ በክርስቶስ መንፈስ እንደ ገና ተወልደህ ከሆነ ለመመለስ እንኳ ብትሞክር አይቻልህም በአንተ ያለው ሕይወት የድሮው ከሆነ ግን የክርስትና ሃይማኖት ከምታስንቅ ቶሎ ወደሚለውጠው ኢየሱስ ብትመጣና ብትለወጥ ይሻልሃል ። ለጥፋት ሥጋውንና ደሙን ሳይገባህ አትውሰድ አስቀድመህ ራስህን መርምር ከዚያም ውሰድ ።

## መዳን በሌላ ስም የለም ።

በኃጢአት ለመኖር ብትፈቅድ ግን የኃጢአት ደመወዝ ሞት ስለሆነ መጨረሻህ ጥፋት ይሆናል የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ( በሌላ ሰው ወይም በሙላእክት ወይም በገንዘብ ሳይሆን ) ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው ። ሮሜ ፮ ፡ ፳፫ « መዳንም በሌላ በማንም የለም ፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና » (ከተሰቀለው ከክርስቶስ ኢየሱስ ) በቀር የሐዋርያት ሥራ ፬ ፡ ፲፪ ።

« እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞ ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ። ተመለሱም » ( የሐዋርያት ሥራ ፫ ፡ ፲፱—፳) የሚለውን የመንፈስ ቅዱስ ቃል ብትቀበለው መልካም ይሆንልሃል ። ሰው ካልተመለሰ ከነበረበትም ደረጃ ወደ ክርስቶስ ካልመጣ የመጨረሻ ዕድሉ የዘላለም ሞት ነው ።

አንተም ካለህበት ግማታምና ሰላም የሌለው የብስጭት ኑሮ በንስሐና ከልብ በሆነ ልቅሶና ፀፀት ወደ ክርስቶስ ብት መለስ የሰላም ጌታና አምላክ በቅጽበት ሊረዳህ ዝግጁ ነው ። ተመለስ እንደእሪያ በሚገማው ቦታ አትንከባለል ፡— ክርስ ቶስ ከዚያ አርነት አውጥቶሃል ። ለተቀበሉት ሁሉ ሰላም ነው በልብህ ሰላም ይሞላል ።

በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን ፡—

«እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ» እያለ ይለምንሃል ። ገላትያ ፭ ፡ ፩ ሰላም ከሚያሳጣህ ሁሉ ነፃ ሁን ።

ከሆነው ዓይነት ሃይማኖት አንዱን መርጠህ ማኅበርተኛ ብትሆን ወይም ከዕገሌ ሃይማኖት ነኝ የዚህ ሃይማኖት አባል ነኝ እያልክ ብትፎክርና ብትመካ መንግሥተ ሰማያት አትገ ባም ። አስተውል ክርስቶስ ወደዚህ ሃይማኖት ኑ ወደዚያ ሃይ ማኖት ሂዱ የኛ ሃይማኖት ነው ጥሩ ብላችሁ አስተምሩ አላ ለም ጌታ የአንድ ወይም የሺህ ሃይማኖትን መያዝ እንደማያ ድን አውቆ ፻፲፱ ዓመት ተከል «ወደእኔ ኑ» «እኔ የሕይወት ውኃ ነኝ» አትጠሙም » ወደ እኔ ኑ «እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ » አትራቡም ። «ወደ እኔ ኑ » «እኔ የሕይወት መንገድ ነኝ » አትጠፉም «ወደ እኔ ኑ » «እኔ መልካም እረኛ ነኝ» ተኩላ አይነጥቃችሁም ከእጄ ማንም አይወስዳችሁም ። «ወደ እኔ ኑ » «እኔ የሕይወት ቃል አለኝ » ለሥጋችሁ ፈውስ አጥ ንታችሁንም ጠጋኝ ነውና « ወደእኔ ኑ » እኔን ያገኘ ሕይወትን አገኘ እያለ ሕዝቡን ይጠራ ነበር ። አሁንም በቃሉ እየጠራ ነው ።

እንመጣም ፡ እንሰማም ፡ ሃይማኖት ይሻለናል ፡ አብርሃም ያመጣው ፡ ሙሴ ያስገኘው ፡ ዶክትሪን ያመጣው ይሻለናል ላሉት ግን ሲነቅፋቸው እንዲህ አለ ፡—



« ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል » ማር. ፯ ፡ ፮—፯ ፤

በሌላ በኩል ደግሞ ስለሃይማኖተኞች ሲናገር «በውጭ ያሉት ግን አይተው እንዲያዩ እንዳይመለከቱም ሰምተውም እንዲሰሙ እንዳያስተውሉም እንዳይመለሱ ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸው ነገር ሁሉ በምሳሌ ይሆንባቸዋል ። » ይላል ማር. ፬ ፡ ፲፪ ፤

እነዚህ ሰዎችና አንተም እንዲህ ያለውን ታላቅ ኃጢ አት በክርስቶስ መዳን ቸል ብትሉት እንዴት ታመልጣላችሁ ይህ በጌታ መጀመርያ የተነገረ ነበርና ። ዕብ. ፪ ፡ ፫ ፣

## እነርሱ አንድ ይሆኑ ዘንድ ።

በሃይማኖት እንደምንለያይ የኔ ይሻላል ፤ የኔ ይሻላል በመባ ባል በትዕቢት እንደምንበታተን ጌታ ያውቅ ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን ወደአብ ሲጸልይ እንዲህ አለ «ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለእነዚህ ብቻ አለምንም አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ ። እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥ ቻቸዋለሁ » ዮሐ. ፲፯ ፡ ፳፩—፳፫ ፤

ቤተ ክርስቲያንህ ወይም ማኅበርህ ይህንን ጸሎት ለምን ጌታ እንደጸለየው ታውቃላችሁን ? መለያየትን አብልጣ ታም ናለች ? ስብከትዋ የመለያየትን መንፈስ ያዘለ ነውን ? ጥምቀ ትን ብቻ ወይም የግልዋን እምነት ( ዶክትሪን ) ታስፋፋለችን ? ክርስቶስን ረስታ እንደ ባዶ የቆርቆሮ ዕቃ በብላሽ ትጮሃለች? አስተማሪዎችህና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችህ በሥጋ ዕው

ቀት የተሞሉ ቃላት እየወረወሩ የሰውን ነፍስ ዕረፍት ያሳጣሉን ? የእግዚአብሔር ቃል ግን መንፈስ ነው በመንፈስም ካልሆነ በቀር በሥጋም ጥበብ ወይም በሃይማኖት ትምህርት ( በቲዮሎጂ ) ሊመረመር አይቻልም ። አንዳንድ መለውጥ ወይም እንደገና መወለድ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች በልዩነት ምክንያት ወዴት ሔደው ክርስቶስን ማግኘት እንደሚችሉ ስለጨነቃቸው በኃጥአን መንበር ውስጥና በዋዘኞች ወንበር ላይ ተቀምጠው ሲዳሩና ሲደንሱ ነገር ሲጨልጡ ይውላሉ ። የእግዚአብሔር ቁጣ በትክሻቸው ላይ ነው ።

የሚሻለው ፣ ሁሉ ፣ ሰውን ወይም የሃይማኖት ልዩነትን ሳይ መለከት ወደክርስቶስ በልብ ፀፀት ተመልሶ መዳን ብቻ ነው ክርስቶስ ከእርሱ ጋር እንድትተባበር ይፈልግሃል ። ልዩነት የለም ፤ ክርስቶስ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ እንደሆነ የሚያምን ሁሉ ግን ወንድምህ ነው አትጥላው እንዲሁም ማንንም አትጥላ ።

ያንተም ቤተ ክርስቲያን ሆነች ሌላይቱ በወንጌል ትእዛዝ ካልተመላለሰች በእርግማን ውስጥ ናት ፤ ከራስዋ ባል ቃል ይልቅ የጎረቤትዋን ወንደላጤ ቃል የምትታዘዝ ሴት አመንዝራን ትመስላለች ። ቤተ ክርስቲያንም የጌታን ቃል ስለማትሰማ በልዩነት ታምናለች ፤ ከወንጌል ቃል ተለይታ የዘመኑ ቲዮሎጂ በመራት መሠረት እንዲህ ያለ ነገር በቤተ ክርስቲያናችን ቢኖር ምናልባት በሚል አስተያየት ራስዋን ታረካለች ጌታ ግን ይህን አስቀድሞ ስለተገነዘበ አንድ ሁኑ በወንጌል ብቻ እመኑ እያለ ጨርሶ ሰበከ አሁንም አንድ እንሁን ። በዶክትሪን ምክንያት መለያየትና ውድቀት እንደሚከተል ጌታ በትንቢተ ኢሳይያስ ፳፰ ፣ ፲፩—፲፫፡ ገልጾ ነበር ። ስንጨቃጨቅና ስንነካከስ በድንገት ጌታችን እንዳይመጣብን አስቀድመን ፍቅርንና አንድነትን እንያዝ ።



## ከተመሠረተው በቀር ሌላ የለም ።

ከተመሠረተው በቀር ሌላ መሠረት የሚመሠርት ሐዋርያ ወይም ነቢይ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎዋልና ገላ ፩ ፣ ፰፡፱ ፤ ፩ኛ ቆሮ ፩ ፣ ፲፡፲፩ ። የክርስትና ሃይማኖትህ መሠረት ከተገለጸለት ከሐዋርያ ጳውሎስ መሠረት የተለየ ከሆነ አንድ ቀን ይገለበጣል ። የጌታ ቃል «የማያስተውል ሕዝብ ይገለበጣል» ይላልና ሆሴዕ ፬ ፣ ፲፬ ። እንዳትገለበጥ ያለህበት ቤት መሠረቱን መርምር !!

በዚህ ነገር እንድታስብበት ጌታችን የበለጠ ማብራሪያ ከቃሉ ይሰጥሃል። «ወደኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም ሰምቶ የሚያደርገው ማንን እንዲመስል አሳይችኋለሁ ። ቤት ሲሠራ አጥልቆ የቆፈረ በዓለት ላይም የመሠረተ ሰውን ይመስላል ። ጐርፍም በመጣ ጊዜ ወንዙ ያን ቤት ገፋው በዓለት ላይም ስለተመሠረተ ሊያናውጠው አልቻለም ። ሰምቶ የማያደርገው ግን ያለ መሠረት በምድር ላይ ቤቱን የሠራ ሰውን ይመስላል ወንዙም (የፍርድ ቀን) ገፋው ወዲያውም ወደቀ የዚያ ቤት አወዳደቅም ታላቅ ሆነ » ይላል ። ሉቃ ፮ ፣ ፵፯—፵፱ ፤

ስለ ቤተ ክርስትያናችሁና ስለሥራህ መሠረት በየትኛው እንደሆነ አሁን ማረጋገጥ አለብህ የማያስተውለው ሁሉ የቁጣ ማዕበል ሲመጣበት ይገለበጣል ። ከተመሠረተው ሥርዓት በቀር ሌላ መሠረት ሊቅ ነኝ ብሎ የሚመሠርት ሁሉ በቀኑ መጨረሻ ይገለበጣል ፤—በቃሉ የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ክርስቲያን ቀኑ ሲደርስ ይገለበጣል—ታላቅና አስፈሪ ቀን ይደርስበታልና ።

ግልጽ ሁኖ እየታየው እንዲህ ይመስለኛል፣በዚያ ጊዜ በዚህ ጊዜ እያለ የሰማያዊ ጌታን አረፍተ ነገሮች የሚያፋልስ ሰው ሁሉ ወዮለት ቀኑ ሲደርስ በከባድ ቅጣት ውስጥ መግባቱን ይገንዘብ ፣ ቃሉ ግን እውነት ነው ።

ዕቢተኞች ወገን እንዳትሆን ከእንቅልፍህ ተነሣና ለመቅረዝህ ዘይት ከሰማያዊ ጌታ ተቀበል።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ደግሞ በመቅረዛቸው ዘይት ሳይኖር ባዶ መቅረዝ ይዘው ይመካሉ፡- እንደነሱ ባዶ እንዳትሆን ቶሎ መቅረዝህን አንቀሳቅስና መርምር ፤ ዘይቱ መንፈስ ቅዱስ በላይህ ላይ ቆሞ እንዲሞላህ ይጠብቃል ልታደርገው የሚገባህ መቅረዝህን ማለት ልብህን አስፍተህ መክፈት ብቻ ነው። ያኔ ትሞላለህ ፤ ታበራማለህ ብርሃንህም በሰው ሁሉ የበራ ይሆናል።

«ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» ይላል የጌታ ቃል ፩ኛ ቆሮ.፲፡፲፪ አንተም በተቀበልከው መክሊት ተጠንቀቅ ከሰማኸው ምናልባት እንዳይወስድብህ መርምር።

## የእግዚአብሔር መኖሪያዎች ።

ክርስቲያን የክርስቶስ መኖሪያ ወይም የክርስቶስ ማኅደር እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ፡- «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል ፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም ይላልና። » ዮሐ.፲፬ ፣ ፳፫ ፤

የክርስቶስ ማኅደር ከሆነ ደግሞ በውስጡ ላለው መታዘዝ አለበት አንድ ማኅደር ለአንድ መጽሐፍ ስፍራ እንዲሆን ተለክቶ ከተሠራ በኋላ ፤ ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ ጨምሮ ለማስገባት አይቻልም ። እንዲሁም እኛ የክርስቶስ የቅዱሱ ማደርያ ከሆንን በኋላ በርኵሰትና በትዕቢት መሞላት የለብንም ። በሙላቱ መኖር አለብን ።

« እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ። እቀጣችሁም አለሁ።እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ።እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ። ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ ፤ ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀ



መጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ ፤ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ ። » ይላል ክርስቶስ ፤ ራእ.፫ ፣ ፲፱-፳፪

በራእየ ዮሐንስ ከምዕራፍ ፪ እስከ ምዕራፍ ፫ ያሉትን የሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት ምሳሌ ተመልክተህ ከየትኛው እንደሆንክ ራስህን መመርመር አለብህ ። ወደ ግራና ወደቀኝ ሳትል ቃሉን የምትጠብቅ ከሆንክ በእርግጥ በሩ አይዘጋብህም ። በመጨረሻም ቀን አታፍርም እንግዲህ ለአብያተ ክርስቲያኖች የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ እያለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር (ራእ. ምዕ ፪-፫) ተመልከት ።

በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ቅርንጫፎች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል ፤ በውስጣቸው ያለው የሰላም ማነስ ጉዳይ ግን ከብዛታቸው በላይ ነው ፤ የቤተ ክርስቲያኖች ሽማግሌዎች ታላላቅ ናፖሊዮኖች ናቸው ። የእነርሱም የራሳቸው ካልሆነ በስተቀር መልካም ቢሆን ከፉ ከተራ ማኅበርተኛ አሳብ ወይም ምክር ሆነ አስተያየት አይቀበሉም ። ከአፋቸው የሚወጣው በመንፈስ የተቀመመ መሆኑ ቀርቶ የእግዚአብሔር ቃል የሌለው እንደጭንቁር የሚመር ነው ። በዚህ ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ሰላም የተበላሸ ነው ። የእግዚአብሔር መኖሪያ የነበረው ልብ የሥጋና የሰይጣን ፈቃድ በመፈጸም የርኩሰት መደብር ይሆናል ።

## አንድነትና ፍቅር ጠፋ ።

« እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም » ዮሐ. ፲፭ ፣ ፲፪-፲፫ ። እኛም ስለወንድሞቻችን መሞት ይገባናል ።

እርስ በርሷ የማትዋደድ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ አይደለችም ።

ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ፡— «ነገር ግን ወን
ድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ
ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያ
የት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም እለምናችኋለሁ ።» እያለ ነዋሪ ልመናውን ወደ እናን
ተም ይልካል ፩ኛ ቆሮ. ፩ ፥ ፲ ፤

የአንድ አባት ልጆች ሁነን በሚፈርስ ድንጋይ በተሠ
ራው ቤት የክርስቶስን ወንጌል ልናሰማበት ፍቀዱልን ብለን
ስንለምናቸው ከየት ነህ ? ከኛ ማኅበር ካልሆንክ አንፈቅ
ድም ይሉናል ፡— ክርስቶስ ግን በየማኅበሩ ልዩነትን ስበኩ
ብሎ አላዘዘም ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ አንድ ልብ
እንዲኖራቸው ለሰማይ መንግሥት እንዲዘጋጁ የወንጌልን
ቃል አንድ ሳያስቀሩ እንዲጠብቁ አስተምሩ ከጨለማም ወደ
ብርሃን አውጥዋቸው አለ እንጂ ።

ከጨለማ ማኅበር ወጥተን ( ከሰይጣን ) የክርስቶስ የሰ
ማያዊት ቤት ማኅበርተኞች ነን ወንጌልን ብቻ እንጂ ማሕ
በሮችንና ልዩነታቸውን አንሰብክም ቢሉዋቸው ያልተጠሩ
በትን ስም ይሰይሟቸውና አሃ ! ከ— ከማኅበር ነህ መሰለኝ
እያሉ ያሽሟጥጡዋቸዋል በትዕቢት መንፈስ ተሞልተው የእ
ግዚአብሔር ሰላምታ እንኳ ሳይቀር ነፍገውዋቸው ይሄዳሉ ።
ይህ ስለምን ይሆን ? ከትምህርት ማነስ ነው ወይስ ከትዕቢት
ብዛት ? ከእነዚህ አንዱ አለ ።

ይህም ቢሆን የክርስቶስን ጸሎትና የእግዚአብሔርን መንፈስ
ቅዱስ በትሕትና ስለአንድነታችን መለመን አምንበታለሁና
መንፈስ ቅዱስ በእናንተና በእኛ በወረደ ጊዜ የአንድነትና
የመስማማት የፍቅርንም ሐረግ እያንዳንዳችን ሳያሥር አይቀ
ርም ።



የመንፈስ ፍሬ ማለት ፍቅር ፥ ደስታ ፥ ሰላም፥ትዕግስት ቸር
ነት ፥ በጎነት ፥ እምነት ፥ የውሐት ፥ ራስን መግዛት በአሁኑ ጊዜ
ስለሚያስፈልጉን በጾምና በጸሎት በብርቱ መሻት ይገባናል ።
ገላ. ፭ ፥ ፳፪ የተጠቀሱት ዘጠኝ ነገሮች በሐዋርያት ዘንድ ስለ
ነበሩ ቤተ ክርስቲያን ለመቆም ቻለች ጽናትም ነበራት ።

ጌታ ሐዋርያትን ሲያዛቸው አስቀድማችሁ እርስ በርሳ
ችሁ ተዋደዱ ብትወዱኝ ይህን የማዛችሁን የእርስ በርስ መዋ
ደድ ትዕዛዝ ጠብቁ እያለ አስጠነቀቃቸው ። ከዚያም ቀጠለና
በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አዘዛቸው «አብ የሰጠውንም የተስፋ
ቃል ጠብቁ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥ
ቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ ።» ሉቃ
፳፬ ፥ ፵፱ ፤ የሐዋርያት ሥራ ፩ ፥ ፬—፭ ፤

እንዲሁም ኢየሱስ « ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው ።»
ከትንሣኤው በኋላ ዳግመኛ «ሰላም ለእናንተ ይሁን ።» ካለ
በኋላ « አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው
ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ።»
ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በፊት ነበረ ዮሐ. ፳ ፥ ፳፩-፳፪፤
ታላቅ ሰላም በልባቸው እንደፈሰሰና አንድነትንና ፍቅርንም
እንደነበራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል ።

ዛሬ ግን አንድነትና ፍቅር በመጥፋቱ ምክንያት መን
ፈስ ቅዱስ ለመሥራት አልቻለም በልዩ ልዩ ነገሮች ያንጸባ
ረቀች ዓለም የእግዚአብሔርን ፍቅር ከቤተ ክርስቲያን ስለ
ተነጠቀች በመንፈስ ቅዱስና በፍቅር በአንድነት ፈንታ ደረቅ
ጭቅጭቅ በፈረሰ ቤተ ክርስቲያን ቀረ ። ፍቅርና አንድነት
ጠፉ ውድቀትም በዛ ።

ቤተ ክርስቲያን ! መንግሥተ ሰማያትን ትፈልጊያለሽ
ወይስ በዚህ ዓለም ያለውን ሹመት ? ቆይቶ ውርደት ይመጣ

ብሻልና ተነሺ ንስሐም ግቢ እዞኝ አልቅሺም ራስሽን አዋርደሽ በልብ ጸጸት በጾም ወደ ጌታ ተመለሺ በደሙም ታጥ በሽ ከእድፍ ነጽተሽ ተቀደሺ ። ያለ ፍቅር ሁሉ ከንቱ ነው ከእግዚአብሔርም አንድነት የለምና ፍቅር በልብሽ ሞልቶ ይፍ ስስ ።

## የአብን የተስፋ ቃል ተቀበል ።

### የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ።

« ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን ? » የሐዋ. ፲፱ ፡ ፪ ፤ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ባመና ችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን መቀበላችሁና አለመቀበላችሁን እንድታረጋግጡ ይጠይቃችኋል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ፡ «እነሆም አባቴ የሰጠውን የተስፋ ቃል እኔ እልክላችኋለሁ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ » ሉቃ. ፳፬ ፤፵፱ «ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ። መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳ ሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ » የሐዋርያት ሥራ ፩ ፥ ፬—፭፥ ፰ ፤

ይህን ቃል አስተውለህ እንብበኸው ከሆነ ለአንተም ነው ። እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ሥጋ ለለበሱ ሁሉ እንደሆነ በሚ ቀጥለው ምዕራፍ ተመልከት « እግዚአብሔር ይላል በመጨ ረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያል





የእግዚአብሔርን ቃል ሲያዳምጡ ።



የእግዚአብሔርን ቃል ሲያዳምጡ ።

ይህንን ግልጽ ነገር የማይገነዘብ ሰው ፍጹም የለም በቃሉ ላይ ካመጿ ግን ለአመጸኛው ወዮለት ቃሉ ነዋሪና ሕያው ፈራጅ ነውና ።

## መንፈስ ቅዱስ ከውኃ ጥምቀት በፊት ።

የውኃ ጥምቀት ከመቀበሉ በፊት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መቀበል ይችላል ወይ ? አዎ « በቂሣርያ ኢጣሊቄ ለሚሉት ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁልጊዜ የሚጸልይ ነበረ ። ከቀኑም ዘጠኝ ሰዓት ያህል ቆርኔሌዎስ ሆይ የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ በራእይ በግልጥ አየው » « መልአኩም አለው ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ ። አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎች ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን አስመጣ እርሱም አንተና የቤትህ ሰዎች ሁሉ የምትድኑበትን ነገር ይነግርሃል አለው ። »

« ጴጥሮስም ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ስላፈሰሰ ተገረሙ ፤ በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርን ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና። በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ እነዚህ እንደ እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ውኃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማን ነው? አለ» በዚህ ነገርም ተደንቆ «ዮሐንስ በውኃ አጠመቀ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለውም የጌታ ቃል ትዝ አለኝ» አለ ። የሐዋ. ፲ ፥ ፩—፬ የሐዋ. ፲፩ ፥ ፲፫—፲፬—፲፮ ፤ የሐዋ. ፲ ፥ ፵፬— ፵፰ ፤



በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው ።

ታስተውላለህን ? የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለሚታዘዙ ነው ቆርኔሌዎስ እግዚአብሔርን የሚወድ ቅንና ታዛዥ ሰው ነበር በውኃ ለመጠመቅ ወደወንዝ እስኪወርድ አላስቆየውም የልብ ፍሥሐ የሚሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አስቀደመለት ፦ ቤቱም የደስታና የሐሴት ድምጽ እንዲያስተጋባ አደረገለት ከዚያ በፊት የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ የነበረው ጴጥሮስ እንኳ እስኪደነቅ ድረስ አፈሰሰለት አንተም ታዛዥና ቅን ብትሆን ጌታ አልተለወጠምና ሊያጠምቅህ ዝግጁ ነው ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታ ፊትን አይቶ እንደማያደላ ፩፻፲፱ ጊዜ ተጽፎዋል ፤ ከእነዚህም አንዱን ልስጥህ ፦ «ጴጥሮስም (ለመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ) አፉን ከፍቶ እንዲህ አለ፦ እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደሆነ በእውነት አስተዋልሁ ። » የሐዋ. ፲ ፥ ፴፬— ፴፭ ፤

አንተም እግዚአብሔርን የምትፈራና ጽድቅን የምታደርግ ከሆንህ ለመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ የፈሰሰውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አፍስሶ በልዩ ልዩ ልሳንና ምስጋና ሊሞላህ ይችላል ። አይችልም ብትል ጠማማ ነህ ቃሉን አታጣምም የቀናውን ነገር አስብ ጠማማ ዶክተሪን የተማረ የጌታን ቃል ከሚያጣምም ሰው ሰምተህ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት አትናቅ የአብን ስጦታ ብትንቅ ለዘላለም የተናቅህ ሁነህ ትቀራለህ ።

## የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንዴት ልቀበል ?

« አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ » የሐዋርያት ሥራ ፩ ፥ ፬ «ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ»